የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 61
ADDIS ABABA 9th September, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፩/፪ሺ፩ ዓ.ም

የከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፱፻፲፩

CONTENTS

**Proclamation No. 651/2009**

Transaction of Precious Minerals Proclamation …..Page 4911
Corrigendum No. 5/2009 …….. Page …4930
Corrigendum No. 6/2009 …….. Page …4930

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፩/፪ሺ፩

## የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር ራሱን የቻለ የሕግ ማእቀፍ የሚያስፈ-ልገው ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብ-ሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፩/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 651/2009

## A PROCLAMATION TO PROMOTE AND REGULATE TRANSACTIONS OF PRECIOUS MINERALS

**WHEREAS**, the promotion and regulation of transactions of precious minerals require a separate legal frame work;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Transaction of Precious Minerals Proclamation No.651./2009".

## ፪/ ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የከበሩ ማዕድናት" ማለት እንደ ወርቅ፣ ፕላቲንየምና ብር ያሉ ብረት ነክ ማዕድናት እና እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኤሜራልድ፣ ሳፋየርና ኦፓል የመሳሰሉ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት /ጌጣጌጥ ማዕድናት/ ሲሆን ሚኒስቴሩ በመመሪያ የከበሩ ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸውን ይጨምራል፤

፪/ "ግብይት" ማለት የከበሩ ማዕድናትን ወይም የከበሩ ማዕድናትን ውጤቶች ለንግድ ዓላማ ለመግዛት፣ ለመያዝ፣ ለማጓጓዝ፣ በእደጥበብ ሞያ ለማዘጋጀት፣ ለማጣራት፣ ለመሸጥ ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፤

፫/ "እደጥበብ" ማለት በስሚዘሪ ወይም በላፒዳሪ የከበሩ ማዕድናትን የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዲይዙ ለማድረግ የሚያስ-ችል ተግባር ነው፤

፬/ "ሰሚዘሪ" ማለት የከበሩ ብረት ነክ ማዕድ-ናትን ለተጠቃሚዎች ፍጆታ በሚሆን መልኩ ማቅለጥ፣ ቅርጽ ማውጣትና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን ነው፤

፭/ "ላፒዳሪ" ማለት የከበሩ የጌጥ ማዕድናትን የመጨረሻቸውን ቅርጽ እንዲይዙ ለማድ ረግ የሚከናወን የመቁረጥ፣ ቅርጽ የማው ጣት፣ የማለስለስና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ማከናወን ነው፤

፮/ "ማጣራት" ማለት የከበሩ ብረት ነክ ማዕ ድናትን ጥራት ለመጨመር ከውስጣቸው ያለውን አላስፈላጊ ንጥረ ነገር ማስወገድ ወይም አብረው ያሉ ተያያዥ ማዕድናትን ለመለየት የሚደረግ የማንጠር ሥራ ነው፤

፯/ "የግል መጠቀሚያ" ማለት የመጨረሻ ቅርፃቸውን የያዙ የከበሩ ማዕድናትን ለንግድ ላልሆነ አላማ በግለሰብ መያዝ፣ ማጓጓዝ፣ ከሀገር ማውጣት ወይም ወደ ሀገር ማስገባት ሆኖ መጠኑ፡-

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "precious minerals" means metals such as gold, platinum and silver and precious and semi-precious stones (gem stones) such as diamond, rubies, emeralds, sapphires, opal, and includes other minerals as the Ministry may, by directives, so designate;

2/ "transaction" means any activity related to the purchase, custody, transport, crafting, refining, sale or export of precious minerals or products of precious minerals for commercial purposes;

3/ "crafting" means the processing of precious minerals into finished products by means of smothery or lapidary;

4/ "smithery" means smelting, molding and other similar activities of metallic precious minerals to the end product for the use of customers;

5/ "lapidary" means the cutting, molding, polishing and any other similar activities carried out on precious stones to shape them to be ready for use;

6/ "refining" means the process of taking out of impurities or separation of different associated metals from any metallic precious minerals to increase their carat amount or purity;

7/ "personal use" means the custody, transport, export or import of precious minerals by individuals for non commercial purposes which are in their final shape ready for ornamental purposes which may not exceed:

ሀ/ ወርቅና የከበሩ ብረት ነክ ማዕድናት ሲሆን ከ፩፻ ግራም፣

ለ/ የከበሩ የጌጥ ማዕድናት ሲሆን ከ፴ ግራም፣

ሐ/ በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን ከ፩፻ ግራም፣ የማይበልጥ ይሆናል።

፰/ "ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም የከበሩ ማዕድናት ግብይት ፈቃድ ነው፤

፱/ "ፈቃድ ሰጭ ባለሥልጣን" ማለት እንደ አግባቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተ የክልል መንግሥታት ሲሆኑ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ በተመለከተ ሚኒስቴሩ ይሆናል፤

፲/ "ሚኒስቴር" ማለት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤

፲፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፪/ "ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፲፫/ "የበጀት ዓመት" ማለት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ ፩ ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴ ያለው ጊዜ ነው።

፲፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፤

፲፮/ "የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት" ማለት ማንኛውም አመልካች ንግድ ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆኑ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው።

a) 100 grams for gold and other precious metals;

b) 30 grams for precious stones;

c) 100 grams for semi precious stones.

8/ "license" means any precious minerals transaction license issued pursuant to the provisions of this Proclamation;

9/ "licensing authority" means the appropriate regional organ with respect to the licenses referred to in sub-article (1) of Article 5 of this Proclamation and the Ministry with respect to the licenses referred to in sub-articles (2) and (3) of the same Article;

10/ "Ministry" means the Ministry of Mines and Energy;

11/ "region" means any Regional State referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

12/ "Bank" means the National Bank of Ethiopia;

13/ "budget year" means the budget year commencing from July 1st and ending June 30th according to the Ethiopian Calendar;

14/ "person" means any natural or juridical person;

15/ any expression in the masculine gender includes the feminine;

16/ "Certificate of Competence" means a permit issued by the Ministry to approve the capability of an applicant for trade license.

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ ማናቸውም የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪/ አግባብ ባለው የማዕድን አዋጅ መሠረት ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ሰው ያመረተውን ማዕድናት በሀገር ውስጥ ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመሸጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አያስፈልገውም።

## ክፍል ሁለት
## ስለ ከበሩ ማዕድናት ግብይት ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት

## ፬. የፈቃድ አስፈላጊነት

ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ቀርቦ በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበና በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የጸና ፈቃድ ሳይኖረው የከበሩ ማዕድናትን ግብይት ማካሄድ አይችልም።

## ፭. የፈቃድ ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ፈቃዶች ይሰጣሉ፡-

፩/ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪነት ፈቃድ፤
፪/ የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ፈቃድ፤
፫/ የከበሩ ማዕድናት ማጣራት ፈቃድ።

## ፮. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች ይሰጣሉ፡-

፩/ የከበሩ ማዕድናት ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣

፪/ የከበሩ ማዕድናት ላኪነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት።

## 3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply to govern the conduct of all transactions of precious minerals with in the territory of Ethiopia.

2/ Any person who has been issued a licensee in accordance with the appropriate mining laws is not required to have a certificate of competence or license pursuant to this Proclamation in order to sell locally or export abroad the precious minerals it produces.

## PART TWO
## PRECIOUS MINERALS TRANSACTION LICENSES AND CRTIFICATE OF COMPETENCES

## 4. Requirement of License and Certificate of Competence

No person shall carry out the transaction of precious minerals unless he is registered in the appropriate government office and is a holder of an appropriate and valid license or Certificate of Competence as appropriate.

## 5. Types of Licenses

The following licenses may be issued pursuant to this Proclamation:

1/ precious minerals brokerage license;
2/ precious minerals crafting license;
3/ precious minerals refining license.

## 6. Types of Certificate of Competence

The following Certificate of Competence may be issued pursuant to this Proclamation:

1/ Precious Mineral Trade Certificate of competence,

2/ Precious Mineral Export Certificate of Competence.

## ፯. የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪነት ፈቃድ

የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪነት ፈቃድ የከበሩ ማዕድናትን የመግዛት፣ ለሽያጭ የመያዝ፣ የማዘዋወርና በሀገር ውስጥ በባንኩ መመሪያ መሠረት ወዲያውኑ የመሸጥ መብት ይሰጣል።

## ፰. የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ፈቃድ

የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ፈቃድ የከበሩ ማዕድናትን በባንኩ መመሪያ በሚወሰነው መጠን የመግዛት፣ የመያዝና የማጓጓዝ፣ የሰሚዘሪና የላፒዳሪ ሥራ ለማከናወን እና ምርቱን በሀገር ውስጥና በባንኩ መመሪያ መሠረት በውጭ አገር ገበያ የመሸጥ መብት ይሰጣል። የዚህ ዓይነቱን ፈቃድ የያዘ ሰው ከከበሩ ማዕድናት ተመርተው የተበላሹ ወይም የተሰበሩ ጌጣጌጦችን መጠገን ወይም በግዢ መሰብሰብ ይችላል ሆኖም የክንውኑን ሁኔታ በተገቢው መዝገብ መመዝገብና ወቅታዊ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ማቅረብ ይኖርበታል።

## ፱. የከበሩ ማዕድናት ማጣራት ፈቃድ

የከበሩ ማዕድናት ማጣራት ፈቃድ በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ አገር የገቡ የከበሩ ብረት ነክ ማዕድናትን የማጣራት ሥራ የማከናወን መብት ይሰጣል።

## ፲. የከበሩ ማዕድናት ንግድ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት

የከበሩ ማዕድናት ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተገቢውን ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በማግኘት የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ የከበሩ ማዕድናትን በጅምላ ገዝቶ በችርቻሮ በሀገር ውስጥ የመሸጥ መብት ይሰጣል።

## ፲፩. የከበሩ ማዕድናት ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት

የከበሩ ማዕድናት ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተገቢውን ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በማግኘት የሚከተሉትን የከበሩ ማዕድናትን የመግዛት፣ የመያዝ፣ የማጓጓዝና በባንኩ መመሪያ መሠረት ወደ ውጭ አገር የመላክ መብት ይሰጣል፦

ሀ/ የመጨረሻ ቅርጽ የያዙ ወርቅና ብር፣

## 7. Precious Minerals Brokerage License

A precious minerals brokerage license grants to the holder of the license the right to purchase, hold for sale purposes, transport and forthwith sale precious minerals locally.

## 8. Precious Minerals Crafting License

A precious minerals crafting license grants to the holder of the license the right to purchase, hold and transport precious minerals in an amount to be specified by directives of the Bank, carry out smothery or lapidary and sale its product locally or abroad pursuant to the directives of the Bank. The holder of such License may engage in purchase or maintenance of used or broken or damaged jewelleries and report periodically every month about its activities.

## 9. Precious Minerals Refining License

A precious minerals refining license grants the license holder the right to engage in refining precious metallic minerals produced locally or imported.

## 10. Precious Mineral Trade Certificate of Competence

A holder of the Precious Mineral Trade Certificate of Competence upon acquiring the proper trade license from the appropriate government body grants to the holder of the License the right to purchase in bulk and retail sale of finished precious minerals locally.

## 11. Precious Mineral Export Certificate of Competence

A Precious Mineral Export Certificate of Competence upon acquiring the Trade License from the appropriate government body grants to the holder of the Certificate the right to purchase, custody, and Export the following precious minerals pursuant to the directives of the Bank:

a) gold and silver which are in their final shape,